## ከኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት

## የተሰጠ መግለጫ

ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተነጠቀውን ነጻነቱን፣ የተገፈፈውን መብቱን፣ የተራከሰበት አንድነቱን የተደፈረውን ሉአላዊነቱን፣ የተንቋሸሸ ሰንደቁን ያስከብር ዘንድ አቋራጩ ጎዳና፣ የተባበረና የተቀናጀ ሕዝባዊ ክንድ ፣ መሆኑን ለመጠቆም ጭምር ነው ኢሕአፓ ወክንድ ብለን ምስረታችንን ያበሰርነው።

የመመስረታችን ብስራት በቀናት ቢስላ ለጋዎች ልንባል እንችላለን። ይሁንና የብዙ ሺህ ለግላጋ ዴሞክራሲያዊያን ታጋዮች፣ ለዴሞክራሲ ደማቸውን የገበሩ ሰማዕታት ወራሾች ነንና ነገሮችን በጥልቀት እንገነዘባለን። የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሎም የአፍሪካ ቀንድ ሁነኛ ጠላት የሆነውን የወያኔን ሥራዐት በሚገባ በማወቃችንም ጠንክረን ልንፋለመው መዘጋጀታችን መብታችን ብቻም ሳይሆን ግዳጃችን ጭምር መሆኑን በማወቅ ነው። ለዚህም ተመክሯችሁን ላጋራችሁን ድጋፋችሁን ለቸራችሁን ምርቃታችሁን ላልነፈጋችሁን በሙሉ ኢወክንድ ታላቅ ምስጋናውን ያቀርባል

የወያኔ ሥርዐት አሽባሪ በመሆኑ በዚህ ቡድን ስር የምትተዳደር ሀገር የርሐብና የእልቂት ዜና መጨረሻና ገደብ እንደሌለው በሐገሩ ጉዳይ ባይተዋር ላልሆነ ዜጋ ሁሉ ግልጽ ነው። ይሄንን ዘግናኝ ሁኔታ ቁጭ ብለን የምንመለከተው ሳይሆን የሐገሬ ጉዳይ ያገባኛል የምንል ወጣቶች ሕዝባዊ ክንዳችንን አስተባብረን በጋራ እንድንነሳ ኢወክንድ ለመላው ኢትዮጵያዊያን ወጣቶች የትግል ጥሪ ያቀርባል።

ወያኔ ባለፉት 18 አመታት በህዝብና በሀገር ላይ የፈጸመው ወንጀል እንዳለ ሆኖ ሶስት አብይት የሰሞኑ ወንጀሎችን ለመግለጽ ተገደናል።

1ኛ. ከአንድ አመት በፊት ከሁመራ እስከ ጋምቤላ ከ1600ኪ.ሜ ርዝመትና 40.ኪ.ሜ ስፋት ያለውን የኢትዮጵያን ለም መሬት ለሱዳን የሸጠው ወያኔ ዛሬ ደግሞ በኢሕአፓ የሐምሌ 3 መግለጫ እንደተመለከተው ሐምሌ 1/2001 የሱዳን ወታደሮች በኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ላይ ተኩስ ከፍተው ኢትዮጵያዊያንን እንደገደሉና በዚህም ድርጊት ወያኔ ቀጥተኛ ተባባሪነቱን በድጋሚ ማሳየቱን ስናይ፣

2ኛ. ባሳለፍነው ሁለት ሳምንት በወርሐ ሰኔ ኢጋማሽ ወያኔ በካድሬዎቹ አማካይነት በቀሰቀሰው የሐይማኖት ግጭት እንደ ገላጋይ ገብቶ ተኩስ በመክፈት በደሴ ያፈሰሰውን የዜጎች ደም ስንመለከት፣

3ኛ. የፀረ ሽብርተኛ አዋጅ ብሎ እጃቸውን ብቻ እንዲሰቅሉ በተቀመጡ የፓርላማ አባላቱ ያፀደቀው ህግና የአባቶችና የእናቶች የተጋድሎ ውጤት ያፈራውን የሐገሪቱን ሰንደቅ አላማ በማን አለብኝና በእብሪት ተወጥሮ ሊቀይር መነሳቱን ስንሰማ፣ ኢወክንድ ጅቡ ከሚበላህ በልተኸው ተቀደስ የሚለውን የማሳሰቢያና የማስጠንቀቂያ መልእክት እያስተላለፈ የሚከተለውን ጥሪ ያቀርባል።

ሀ. ዋቢ ጠበቃ የሌላችሁ አርሶ አደሮቻችን ለሱዳን ከነ መሬታችሁ ተቸራችሁ በውርደት አንገዛም በማለት የምታደርጉትን የሞት ሽረት ትግል ለማገዝ ኢወክንድ ከጎናችሁ መሰለፉን እየገለጸ በጎንደርና በተጎራባች ክ/ሐገራት የሚገኙም የኢወክንድ አባላት ተገቢውን እገዛ እንዲያደርጉ ጥሪውን ያስተላልፋል።

ለ. ከህብረ ብሔራዊነት አልፎ ህብረ ሃይማኖታዊ መሆኗን ታሪክ የመሰከረላት ኢትዮጵያ በዋቢነትና በግንባር ቀደምትነት ሁለቱ ሃይማኖቶች በእኩልነት ተፋቅረውና ተከባብረው ከሚኖሩባት የሀገራችን ክፍል ውስጥ አንዷ ወሎ ነች። ዛሬ ይህንን

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: join@eprpy.com
www.eprpy.com

በጋራ ተዋዶና ተከባብሮ የሚኖር ሕዝባችንን መሰረት ሊንድ የሚችል ምድራዊ ሐይል ባይኖርም ወያኔ ደም ለማፋሰስ የሚያደርገውን ሙከራ በፅናት ከሕዝባችን ጎን ቆመን መመከት እንዳለብን ለሀገራችን ወጣቶች ጥሪ እናቀርባለን።

ሐ. ትላንት ጨርቃችሁን ማንጠልጠል ትችላላችሁ ብሎ በክቡር ሰንደቃላማችን ላይ የተሳለቀው ወያኔ አልፎም ከጨርቁ ሳይሆን ከበስተጀርባው ባለው መልእክት ላይ ነው ፀባችን ያለን ወያኔ የሐገሪቱን ሰንደቅ አላማ ሐገር ሊያፈርስበት በተነሳበት አርማ ሊተካው አዋጅ ማስነገሩ የኢትዮጵያ ወጣቶች በጭራሽ የማንቀበለውና ይበልጥ የኢትዮጵያን ስንደቅ ከፍ አድርገን የምንታይበት ወቅት መሆኑን በመገንዘብ የኢትዮጵያዊነት ምልክት የሆነውን ከትውልድ ትውልድ የተላለፈልንን ሰንደቅ ዓላማ ከምንግዜውም በላይ እንድናውለበልብ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥሪ እናቀርባለን።

**የኢትዮጵያ ወጣቶች የትግል ገድል ታሪክ ዛሬም ህያው ነው!!!**

**እናቸንፋለን!!!**

ኢወክንድ

ሐምሌ 13 ቀን 2001 ዓ.ም.
July 20, 2009

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: join@eprpy.com
www.eprpy.com